

# ከድጡ ወደ ማጡ!



ወንድሙ መኰንን፣ ሎንደን 4 July 2013

## መግቢያ

በዓለም ዙሪያ የተበተናችሁ ወገኖቻችን በኛ ሎንደን በምንኖረው የኦርቶዶክስ ሀማኖት ተከታይ በሆንን ኢትዮጵያውያን ላይ በአንድ መነኰሴ ነኝ ባይ **የቀበሮ ባሕታዊ** ግለሰብ አማካኝነትና በወያኔ ቀጠረኞች የደረሰብንን ይቅር የማይባል በደል ዕለት በዕለት እንደምትከታተሉና መጨረሻችንን ለማየት በጉጉት እንደምትጠባበቁ እዚህ ያሉት ወንድሞችና እህቶች በሚገባ ያውቁታል። ያመሰግናሉም። ታዲያ ከዚያች ቀውጢ የሁዳዴ ጾም መያዝያ ማግስት፣ ጀምሮ የተዘጋብን ቤተክርስትያን ጉድይ እስካሁን እልባት ሳያገኝ፣ ቀርቶ ሕጻናቱም፣ አይቆርቡም፣ አዛውንቱም፣ ወይዛዝርቱም እግዚአብሔርን ማምለኪያ ቦታ አላገኙም። ይኸ በደል ባንድ ካኽን ንኝ ባይ ሲፈጸም በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪአው መሆን አለበት። ብቻ በየሰንበቱ፣ **"አንድ ሐሙስ የቀራችሁ፣ የእንጨት ሽበት፣ ሽሜ ጉጉ"** እያተባሉ በወያኔ ሶልዲ በተገዙ ስድ ወጣቶች እየተሰደቡ፣ **ሴቶችም ለጆሮ በሚቀፍ ስደብ እየተሸማቀቁ፣** ቤተክርስቲያኗ ቅጥር ገቢ እየገቡ ሕንጻዋን እየተሳለሙ፣ ከሕዝብ ጋር ከሚንከራተቱ **አንድ ቄስ፣ አንድ መሪ ጌታ፣ እና በመምሕር ታሪኩን ጨምሮ በዛ ካሉ ዲያቆናት** መሪነት ሜዳ ላይ እየጸለዩ፣ አራት ወራት አሳለፈዋል። ምን ላይ ደረሰ እያላችሁ የምትጠይቁ በዝታችኋል። ሁለቱ አዋጊ ጳጳሳትም፣ አቡነ ገብርኤልና አቡነ ቀውስቶስ፣ የትም **ቦታ** መንቀሳቀስ በማይገባቸው የሱባኤ ሰሞን አገረ ስብከታቸውን ጥለው ሕንጻውን ሊቀሙን ቢመጡም፣ በተደረገው ርብርብ ሳይሳካላቸው ቀርቶ "አባ" ተባዩን የቀበሮ ባህታዊ፣ "በርታ" ብለው ወደመጡበት ተመልሰዋል። "በመነኰሴ ነኝ" ባዩ አመጻኛ ግለሰብ አዝማችነት፣ ተዝቆ፣ ተዝቆ በማያልቀው የወያኔ ገነዘብ ኪራይ ከፋይነት ተደለለው፣ ቤተክርስቲያን አንድም ቀን ረግጠው በማያውቁ ከየት እንደመጡ የማይታወቁ ጋጠ-ወጦች (ጋንግስተሮች) እስከመገፋት መገፍተር፣ደርሷል። እና አባ ተባዩም ንብረት እስከመስረቅና ማጋዝ ጀምረው ነበር። እንዲያም ሁኖ፣ እስካሁን ሕዝበ ክርስቲያኑ ቤተክስቲያኑን እየጠበቀና እየተከላከለ ይገኛል። ግፉ ግን በዝቷል። ሁለንተናው ዘቅጧል። ነገሩ ሁሉ ከድጡ ወደማጡ ተብሎ ቢደመደም ይበጃል። "አባባሱባት" ነበር ያልኳችሁ ባለፈው? እሱን እርሱት። ያሁኑ ይባስ።

## የመዳን ንሰሐ ለጥቃት ሲያጋልጥ

ባለፈው ሳምንት የተፈጽመው አሳፋሪ ወንጀል፣ በታሪካችን ምንጊዜም "በምዕምን ላይ ደረሰ" ሲባል ተሰምቶም የማይታወቅ ጉድ ነው። ፈረንጆች "Abuse of Trust" ይሉታል። ያመኑት ፈረስ በደንደስ እንደሚሉት ነው። በመጨረሻው ጽሑፌ ከአንባቢዎቼ የተልያየሁት "ብጹዐን አባቶች ለታስታርቁን ወይስ ልታዋጉን መጣችሁ?" በማለት በሞነጫጨርኩት መጣጥፍ ነበር። አባዛኛው መልዕክቱ ቢገባውም፣ ሌሎች ሰዎች ነገሩን እያባባስኩ እንጂ እየረዳሁ አለመሆኔን ስላሳሰቡኝ፣ ላልተወሰነ ጊዜ ምንም ላለመጻፍ አቅጄ ቆየሁ። የኔ ዝምታ ግን "ትሻልን ፈትቼ ትብስና አገባሁ" ቢጤ ሆኖብንና አሸንፈው ጭጭ ያሰኙኝ መሰላቸው። የኔ መተው ነገሩን አልከተተውም። ጳጳሳቱ ወደመጡበት በመመለሳቸው፣ የወያኔን ይሁንታ ተጨምሮበት፣ የቀበሮ ባህታዊው ባሰባቸው። በነጋ በጠባ ሕዝቡን "በምን ላቁስለው?" እያሉ ሲያልሙ የሚያድሩ ይመስላሉ። ፓትርያርኩ በሞቱላቸው ጊዜ፣ ይኸን ሕዝብ በምን ቆሽቱን ላድብን ብለው፣ ለታጋይ ጳውሎስ ፍትሀት አደርጋለሁ ብለው ተነስተው እንደአንጫጩን ይታወሳል። አሁን ደግሞ ሌላ አገኙ። የቤተክርስቲያናችንን መሠረት የናደ፣ እንኳን ከአንድ የአሀይምኖት አባት ነኝ ብሎ ከሚመጻደቅ ይቅርና፣ ከመርካቶ ዱሩየም የማይጠበቅ፣ በጣም የወረደ ተግባር ፈጸሙ። "ቤተክርስቲያናችንን ይጎዳል፣ ዝም በሉ" ለምትሉን፣ ዝምታ ለበጓም አልበጃት፣ ዝም አንልም። ዝም እማ ካልን ዲያብሎስ ይነግሳል። በዓለም ዙሪያ ያሉት ክርስቲያን ወንድሞችና እየቶቻችን የደረሰብንን በደል አውቀው፣ በጸሎታቸው እንዲተባበሩን፣ በደሉ ይታወቅ። የሎንደንማ ሕዝብ በተፈጽመው አስነዋሪ ነገር ተደናግጦ ምን እርምጃ መውሰድ እንዳለበት ግራ ገብቶት ቁጭ ብሏል። አንዳንዱ፣ "ተው ከእግዚአብሔር ያግኙት"ይሉናል። ኤዲያ! እግዚአብሔር በአምሳያው የፈጠረን የምንችለውን አድርገን የማንችለውን ልንተውለት ነው። የምንችለውንም፣ የማንችለውንም ለሱ መተውማ ስንፍና ነው። የተጎዱት ያቃስታሉ። እንዴት ዝም እንላለን? ከመሀላችን አንዳችን ተጎዳን ማለት፣ ሁላችንም ተጎድተናል ማለት ነው። ነውሩን እራሱ ይደብቅ እንጂ እኔ ጫካ አይደለሁም የምደብቅለት። አልደብቅለትም። ያበጠው ይፈንዳ!

የቤተክርስቲያናችንን ሕንጻ እንኳን ቢወስዱት ነገ ፈራሽ ኖራና አሸዋ ነው። ዕመነታችን ካልተናጋ፣ ፍቅራችን ካልተበረዘ፣ አንድነታችን እስካለ አንበገርም፣ ነገ ከዚያ የበለጠ ልንገዛ እንችላለን። ለእውነት በመቆማችንም እንረካለን። በዞህ ዙሪያ፣ ሕመማችን የሚሰማቸው የአሜሪካው ቀሲስ አስተራየ ጽጌ እንዲህ የሚል መልዕክት አስተላልፈውልናል።

> *"ልታሸንፉ የምትችሉት በንብረቱ ተቆጥታችሁ በመነሳት አይደለም። "ወእመ አመግበ ለዝኢኮነ ውእቱ በከመ ነገረነ ወተሰይመ ለመግቦታ፣ ወነዋ ጽሑፍ ዘይቤ ርጉም ውእቱ ዘይገብር ግብረ እግዚአብሔር በሀኬት ወልንታቀብ እምኩሉ*

*ከመግጽ እመንገለ ሐኬትነ፣ እንትርከበ ተዓዳውያነ ትእዛዙ በምክንያተ ፈጽሞ ትእዛዝ ካለዕ በእንተ ዝንቱ ይደልዎነ ካእበ ከመ ኢንጽልአሙ ለዕለ ይንስኡነ በጸልእ ወቀትል በእንተ ምንትኒ እምንዋይነ" (ፍአ፲፣ ፫፻፶፩" የሚለውን የቤተ ክርስቲያናችንን መመሪያ በመከተል ነው።"*

ቀጥለውም ግዕዙን ፈትተው ሲያብራሩልን፣

*"ይህም ማለት፡- መንፈስን ለመመገብ ብቃት የሌለው ሰው፣ ቦታው በሚጠይቀው በመንፈስና በሞራል ልእልና ራሱን ሳያዘጋጅ፣ በሥጋዊ ጥበብ የእግዚአብሔርን ስራ ለመስራት ቢሞክር የተረገመ ይሁን! ከዚህ አይነት መንፈሳዊ አመራር እንራቅ፣ ቤተ ክርስቲያናችን ካዘጋጀችልን መርሆ ውጭ በሥጋዊ ፍላጎትና ስሜት እየተገፋ ሊመራን የሚሞክር ደፋር አንፈልግም። ይህንንም ስንል በሥጋዊ ስሜት መጣብን ብለን አንጠላውም። ከኛ እንዳንዱ ሆኖ አብሮን ሊኖር ከፈለገ እንወደዋለን እንጅ ካንድነታችን ውስጥ አውጥተን አንጥለውም" የሚለውን ከህሊናችሁና ካንደበታችሁ አታርቁ። ይህ የናንተን የሞራል ልዕልና እያሳየ ከቤተ ክርስቲያናችሁ ቀኖና ዝንፍ እንዳላላችሁ ያስረዳል።"*

ከዚያ ንብረት ንጥቂያ በበለጠ አስከፊ ነገር፣ "አባ" ተባዩ <u>የቀበሮ ባህታዊ</u>[1] የሚያንገፈግፍ ግፍ ሰሞኑን ፈጽመውብናል። የቤተክርስቲያናችንን መሠረት የሆነውን፣ የማይደፈር ሥርዓት ከሥሩ አምዘግዝገው ከመሬት አደባይተውብናል። ከዚህ በኋላ ካህን



የማመን የባህላችንን ግንብ ንደውብናል። ሀይማኖታችን አሰድበውብናል። ይኸ መዓት የጀመረው ሰኞ ዕለት ሰኔ ፲፯ ቀን ፪ሺ፫ ነው። አክሴማ በመልበሳቸው፣ ቆብ በመድፋታቸው ብቻ፣ የበቁ ናቸው፣ መንኰሴ ናቸው፣ ሹመት አይደልላቸውም፣ ፍቅረ ንዋይ አያሰናክላቸውም፣ ሥጋዊ ነገር አያምራቸውም በማለት፣ ሥጋ ወደሙን ለመቀበል ሲባል፣ ያለ የሌለውን ኃጢአት ተናውላቸው ንሰሐ የገቡትን፣ የተናዘዙትንም ያልተናዘዙትንም "እገሌ እኮ እንዲህ ሠርቷል፣ እገሊት እኮ እንዲህ ናት" እያሉ ገበናችንን ባደባባይ፣ ያውም በግጥም መዘከዘክ ይዘዋል። "አባ" ተባዩ ሐሳዊ መሲሕ፣ ካህን ሲሆኑ (ሁነው ከነበር) የገቡትን ቃል ኪዳን (ገብተው ከነበር) ናዱት! ከዚህ በኋላ ምን እስኪያደርትጉን ነው የምንሳሳላቸው? በአንድ የሃይምኖት አባትና፣ በምዕምን ልጅ መሀል በእግዚአብሔር ፊት የተገባውን የዕምነት ቃል አፈረካክሰውታል። የነፍስ አባታችን ናቸው ብለው በእነሱና በእግዚአብሔር መሀል "መነኩሴውን" እንደ አማላጅ ቆጥረው የስድስት ወንዶችና የአንዲት እህት የንሰሐ ኑዛዜ መሰል የስም ማጥፋት ወንጀል፣ በጸሐፈ-ትዕዛዛቸው በኩል በግጥም ተጽፎ፣ ነገሩ በበለጠ ለማስመሰልም፣ በአንደኛዋ እህት ስም፣ የኮማንደር አሰፋን ቋንቋ ልዋስና (እሳቸውም ቢሆኑ በጎን ተወርፈዋል) በውስጥ መረብ (ኢንተርነት) በግጥም ናኙት (የዕንቁላል ጦርነት ቁ፡ ፩ እና ቁ. ፪።) ሌሎቻችንም ተራችንን እየጠበቅን ነው። ይሁን ግድ የለም፣ ሰው እንዳይሆን የለም ይባል የለ? ይሁና። ኃጢአቱ በራሳቸው ላይ እንደረመጥ እንደሚነሰነስ ማን በነገራችው? ይኸን ጉድ የሚፈጽሙት ምናልባት "መነኵሴ ንሰሀ አይገባም የሚለውን የመሀይማንን አብባል ተከትለው ሊሆን ይችላል። ንሰሐ ካልገባትና ከዲይብሎስ መንገድ ካልተመለስ እሳቱ ከማይጠፋ ገብቶ ይቃጠላታል። ስለዚህ ጉዳይ ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር እንዲህ ብለው ጿፈዋል።

*"'መነኩሴ ንሰሐ የለውም የሚለው ተለምዶአዊ አባባልም በምጽሐፍ ያልተደገፈ ባሕላዊ ልምድ መሆኑን በጉዳዩ ዙሪያ ጥናታዊ መጽሐፍ የጻፉት ብጹዕ አቡነ ፍሊጶስ ያስረዳሉ*

*'ይልቅስ ከእግዚአብሔር የሚሠወር ኃጢአት እንደማይኖር ሲታወቅ፣ ከሰው ለመሰወር አባ መባልን ሽቶ ጨለማ ለብሶ፣ የብርሀኑን ጨለማው ሲሻው ቢገኝ፣ ግን ንስሐ የሌለው ኃጢአት በስውር ሲሰራ በመኖሩ፣ በራሱ ላይ ታላቅ ኵነኔ ማምጣቱ ነው።'" (ካሕሳይ፣ ገጽ 99)።*

የኛን አገር ሕግ እንኝ። በዚህ በምንኖርባት አገር ሕግ ግን፣ አንድ ወንጀለኛ፣ ቄሱ ጋ ሂዶ ኃጢአቱን ቢናዘዝ፣ በምንም ዓይነት የሀይማኖት አባት የንሰሐ ኑዛዜውን ለፖሊስ፣ መናገር አይጠበቅበትም። ዶክተርም እንደዚህ ነው። ጠበቃም እንደዚሁ ነው። እነዚሁ ሁሉ የሙያ ሥነ-ምግባር (Professional Code of Ethics) ይገዛቸዋል። "አባ" ተባዩ! ሳትገባቸው የእግዚብሔርን ክህነት የተሸከሙት፣ ያቺኑ፣ በቤተክርስቲያናችን የቀረቺዉን አንዲት የመተማመኛ ማኅተብ በጥሰው ከአፈር ደባለቋት። ምዕምናን! እንግዲህ ካህን ካላመን፣ ከዚህ በኋላ ማንን ልናምን ነው? <u>**"ክህነቴን ከሕጋዊው አገር ቤት ከሚገኘው ሲኖዶስ ነው ያገኘሁት"**</u> እያሉ የሚፎክሩብን፣ ሲኖዶስ ይኸንን ቅሌት እያየ ዝም ካላቸው፣ ማንም ከዚህ በኋላ ቤቱን ዘግቶ ኃጢአቱን ለእግዚአብሔር ይናዘዝ

---

[1] የቀበሮ ባህታዊ የሚለውን ቃል ያገኘሁት፣ "ምንኩስና በኢትዮጵያ፣ ትላንትናና ዛሬ" ከሚባለው፣ ካሕሳይ ገብረእግዚአብሔር መጽሐፍ ነው

እንጂ፣ ካህን ላይታመን ነው። በተክርስቲያናችንም ምስጢራችን ለመጠበቅ ችሎታ የላትም ማለት ነው? "አባ" ተባዩ (ግሩም በዕውነተኛው ስማቸው) ይህቺኛው ከክፋት ሁሉ የባሰች ለዲያብሎስ ነፍሳቸውን የሸጡባት 30 ዲናር ናት። የውስጡም ሆነ የውጪው ሲኖዶስ፣ ይኸንን ጉዳይ መርምሮ እኚህን ሰው ውግዝ ከመአርዮስ ካላሏቸው፣ ልጆቻውም ለመሆን አንችልም፣ አባቶቻችንም ሊሆኑ አይችሉም።

ከሁሉ ከሁሉ የገረመኝ፣ አንዷን የወሎዬ ስም ያላትን እህት አዋረድን ብለው፣ ግጥሙ ብቻ ቤት እንዲመታላቸው የዘባረቁት ነው።

«የወሎ ቆራቢ» ተብሎ ሲነገር፤
በአበባ ታወቀ ተረቱ በተግባር፤
ባአመዴ በእስላሙ ቁርባን አይከበር።"

ኧረ ያንተ ያለህ! እንዲያ አዲሶቹ ወያኔ ጌቶቻቸው "ሐብዚ ሐብዚ" ሲሏቸው አማራ ሳይንትንም ወደ ሰቆጣ አስተጠግተው፣ እንደ አላሙዲ፣ ትግሬ ማድረግ ካላማራቸው በስተቀር፣ "አባ" ተባዩ፣ እራሳቸው እስከአነጋገራቸው "ተጿኢኖ"ሲሉ ሰልሚያስነቃባቸው ወሎየነታቸው አልተፋቀላቸውም። እንግዲያስ "የወሎ ቆራቢ፣ ተብሎ ነገር" ሲሉ፣ እሳቸውም የሚሠሩት ስይጣናዊ ተግባር፣ ከዚያ ከዚያ የወረሱት በሾርኒ ሊነግሩን ፈልገው ይሆን?? አለበለዚያማ ስንት ጻድቃን ከወሎ ወጥተዋል። ኧረ ጸሐፈ ትዕዛዛቸውም ከወሎ ነው ይባላል! ለነገሩስ፣ ጸሐፈ ትዕዛዛቸው ባይሆን ተጋድሞ የሳቸው መንገሻ እንደሆን እንጂ እሱ ራሱ አይነግሥም። ጉድ እኮ ነው፣ ያውም ከወልዲያ! በጽሑፎቿ ድባቅ የምትመታቸውን እህት እናብሽቅ ሲሉ እራሳቸውን ስድብ አርገውት አረፉት። እንዲህ ነው ካህን! ትንሽ ዕውቀት አደገኛ ናት። መርፌ ላይ ትጥላለች።

## ከአያያዝ ይቀደዳል

ሌላው አሳፋሪው ነገር፣ እሑድ እለት ሰበከኩ ብለው፣ "አባ" ተባዩ የለፈለፉት ተራ ንግግር ነው! እንዲህ አሉ!

> "እነዚህ፣ ንጉሳችንን የገደሉ!
> ፓትርያርካችንን የገደሉ!
> አገራችንን ገድለው እዚህ ድረስ የመጡ እኛን ቢገድሉ አይደንቀንም"!"

"እኛን" ሲሉ "ንጉስ ነኝ" ብለው ያልሙ ይሆን? ወዴት ጢጋ ጢጋ! ድኃ በሕልሙ፣ ቅቤ ባይጠጣ አሉ?

ይኸን ነገር አንባቢ ከአንደበታቸው ይስማው እንጂ! ነፍስ እኮ ንግግር ናት! ክሽን ያለች የተራራው ሰብካ!

http://www.youtube.com/watch?v=otlM6x8mzWk

የመድኃኔዓለም ያለህ! ይህ ነገር ወያኔ አዲስ ያገኘው መፈክር መሆኑ ነው መሰለኝ? ከዚህ በፊት **ሐረካት ተካሄደብን** ብለው በወያንኛ ተናግረው አልነበር?[2] ለመሆኑ ንጉሡን "እኔ ነኝ የገደልኳቸው" ብለው የተናዘዘላቸው አለን? 18 ደቂቃ ብቻ ነው የሚፈጀው ፊልሙ። ቢያንገሸግሻችሁም አድምጣችሁ ሳታጣጥሟት ወደፊት አትሂዱ። ልዩ ናት። ታድያ ንግግራቸው፣ ከሼክ ከአቡ ሀምዛ ጋር እንዳይምታታባችሁ ተጠንቀቁ። ዕውነቴን ነው። እምልላችኋለሁ። አባ ግርማ ነኝ የሚሉ ጉደኛ አባይ መንኮሴ ናቸው።

የምሬን ግን፣ አሁን እኚህ ሰው እንደዚያ ሲዘልፉን መስቀል ባይይዙ እኮ ጉድ ፈልቶ ነበር። ሼክ አቡ ሐምዛን (حمزة أبـ و المصري) ምስጋና ይንሳው። "አባ" ተባዩን ስብከት በጨረፍታ ያዳመጠ፣ እና በጎን ቪዲዮውን ያየ "አቡ ሀምዛ ከአሜርካን እሥር ቤት አምልጦ ወደ ሎንደን ተመለሰ እንዴ" ብሎ ቢጠይቅ ምን ይደንቃል? የአባ ተባዩን ያክል የመሳደብ ችሎታ ግን ሼክ አቡ ሐምዛ የለውም። ያቺ ከውስጥ የለበሷት ዲዛይነር ሙሉ ልብስ መሆኗ ነው? ያን ቀን ሊሞሽልቁን ተዘጋጅተው ሲመጡ፣ እንደልማዳቸው ሴትና ወንድ የሚገባብትን ድብልቅ ቀን





ጠብቀው ሳውና ገብተው፣ ሽቶ ነስንሰው መጥተው መሆን አለበት። አምሮባቸዋል። "አምረሻል አሉ ተውበሻል" እያሉ አክሊሲያዎቻቸው (እንደ ጆርጅ ኦርዌል፣ የናፖሊዮን የሰለጠኑ ውሾች ብጤ) ዘምረውላቸው ይሆን? ክርስትና እንዲህ ነው ኢንጂ! ያቺ ከላይ የተለበሰችው አክሴማ ከዚያች እልፍ ሲሉ ውልቅ ትልና፣ ከነቆባቸው ሻንጣ ክትት ቢያደርጓት፣ ዲዛየነር ሙሉ ልብሳቸው ብቅ ብሎ ባርኔጣ ጉብ ቢልና የጸሐይ መነጽር ቢገረግዱ፣ ዋና ቴክሶ ሁነው መሽቀርቀርን ማን ከልክሎአቸው! እንዲህ ነው አራዳ፣ የአራዳ ልጅ።

---

[2] http://www.goolgule.com/esatawi-harekat/



እንዲያው ስለሽቶ ካነሳን፣ እስቲ **<u>መጽሐፈ ሕግጋት</u>** **<u>(ፍትሕ መንፈሳዊ)</u>** ምንኩስናን አስመልክቶ ምን ይላል?

*“መነኮሳት መንፈሳዊ ጌጥ ሁሉ ያጊጡ፣ ሴቶችንም አይጎራብቷቸው፣ በገዳሞቻችውና በሌላይቱ ውስጥ ሥጋ አይብሉ፥ እያጌጡ ሽቶ አይቀቡ፣ ከድኳሳ ማስ ወግን በዝናር ወገባቸውን ይትጠቁን ልብሳቸውን በድኳሳ ግምጃ የመናንያን ልብስ ይሁን” (ቁ.361)*

እንዲት ነው ታዲያ አባ ሆዬ እንዲህ የወንድ ሞዴል ይመስል፣ የዲዛይነር ልብስ እየለበሱ፣ ዘመናዊ ቦርሳ እንደጎረምሳ እያንጠለጠሉ፣ የሚሽቀረቀሩት? ሽቶአቸውማ፣ እልፍ ሲሉ ዕውድ ያደርጋል። ሽቅርቅር ሴቶች ምስጋና ይንሳቸው””

የተዘጋውን ቤተክርስቲያን ቁልፍ በኪሳቸው ወሽቀው፣ እንደማንኛውም መግቢያ የጠፋው አማኝ መጥተው እንዲህ ዝንጥ ብለው በር ላይ ሲቆሙ፣ “አቋቋምሽማ!” የሚለውን የጥላሁን ገሠሠን ዘፈን ያስታውሰናል።

አቋቋምሽማ፣ ልብ ያስደነግጣል፣
ፈገግታሽ <u>ግሩም</u> ነው፣ ጭራሽ ነፍስ ያሳጣል።

ጥላሁንን ገሠሠን ልመርጥላቸው አውጥቼ፣ አውርጄ አስቤበት ነበር። የለም! ጥላሁን ይበዛባቸዋል። ድንገት፣ ሲደንሱ አዳልጦአቸው ቢወድቁ፣ የማነው ዕዳው። በጥላሁን ፋንታ፣ እስቲ ሌላ አስመስሎ የሚያንጎራጉርላቸውን ሰው ልፈልግላቸው። አገኘሁ!

http://www.youtube.com/watch?v=7u0x0rMksXQ

ሲበዛ ደግ ነኝ አይደል?

ለንደን በምንገኝ ወንድሞቼ ሰም አንድ ነገር ማለት እፈልጋለሁ። አንደኛ በአሁኑ ሰዓት ግንባር ቀደም ሁነው እኚህን የቀበሮ በሕታዊ የሚጋፈጡት፣ ጌታቸውም ሆነ፣ ዘለዓለም፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ወታደራዊው ደርግ ሲገድላቸው የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ነበሩ። ጊዜው “አባ” ተባዩ በዕድሜ ደርሰው ወታደር ላለመሆን ገዳም የገቡባት ጊዜ መሆኗን እሳቸውም አይስቷትም፣ እኛም እናቃተልን! የዛሬዎቹ አዛውንት፣ በዚያ እድሜ እንኳን ጠብመንጃ አንስተው ሊተኩሱና መጻፊያ እርሳሳቸውን በቅጡ ከጨበጡ ሶስት ዓመት ቢሞላቸው ነው። ሌሎቻችንም፣ ሻለቃ ማሞን ጨምሮ፣ ገና 12ኛ ክፍል ጨርሰን የወጣን በመሆኑ ንጉሡ ጋ የሚያደርሰንም የለም። እንግዲህ ሁለት በድርግ ዘምን ለጄኔራልነት የበቁ አባቶች አሉ። እንሱ ደግም “አባ” ተባዩን ከሚቃውሙአቸው አዛውንት፣ ወይዛዝርትና ወጣቶች መሀል ከመሆን በስተቀር ቢናግሯቸውም የማይመልሱ አንደበተ ርቱዕ አባቶች ናቸው። በተለይ አንደኛው ጄኔራል፣ ከዚህ በፊት የአቶ ግሩምን ቆብ ያተረፉ ባለውለታቸው በመሆናቸው እንዲህ ዓይነት ስድብ ባልተገባቸው ነበር። እኛ እኛን እንኳን መስደብ፣ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ነውና ተውት።

“ሊገድሉኝ ነው፣ ሰደቡኝ!” እያሉ በመንደር እያውደለደሉ ስም ሲያጠፉ ይውላሉ። እኽ ብለው የሚሰሟቸው ቢኖሩ፣ እነዚያ ጥቂት ያሰለጠኗቸው ወጣት ሴቶቻቸውና መዘምራን ናቸው። ሁሉ ነገራቸው፣ ጨኸቴን ቀሙኝ ነው። ቤተክርስቲያኗን ቁልፈው፣ ቁልፉን በኪሳቸው ተሸከመው እየዞሩ፣ ሳያፍሩ “ፖለቲከኞች ቤተክርስያናችንን ዘጉብን” እያሉ እኮ፣ያለ ምንም ሀፍረት <u>ያወራሉ። እንደ ሕጻን ምስኪን የሆነ እንጂ</u> እንደ <u>“አባ” ተባዩ</u> የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም (ይቅርታ አበባ!)። ምዕምኑን “ዳሽቄ ካልገዛኹህ” የሚሉ ሞገደኛ ሰው፣ እነሆ በገዛ ፈቃዳቸው ቤተክርስቲያናችንን ዘግተውብን፣ ቁልፉን ለወያኔ ወኪሎች በማስረከብ፣ ከአዲስ አበባ ድረስ አቡን በማስመጣት ለመንጠቅ ሞክረው ሕዝቡ ተረባርቦ ስለተጋፈጣቸው፣ የወጣላቸው አንድ ቁጥር ተስዳቢ ወጥቶአቸዋል።

እስቲ ቤተክርስቲያናችንን ከዘጉብን በኋላ የፈጸሙትን በደል አንድ በአንድ እንይ። ወያኔ እምባሲ ስተት ብለው ሂደው ምክርን ከሙሉጌታ አሥራተ፣ ገንዘብን ከወያኔ ሹም ከተለገሱ በኋላ፣ ከአቡነ እንጦንስ ጋር ተመካክረው፣ ሁለት አለብላቢት ወጣት ሲቶችን ፓትርያርኩ ዘንድ ልከው ሁለት ጳጳሳትን፣ አስመጡ። የሚከተለው ፊልም፣ ከዚህ በፊት ያስቀየሟቸውን የታጋይ ፓውሎስ ሲኖዶስን፣ አቡነ ገብሬልና አቡነ ቀውስቶስ በተገኙበት፣ ከአዲስ አበባ ተልከው መጥተው ማርያም ድርሽ እንዳይሉ አስጠንቅቀው የከለከሏቸውን የወያኔውን፣ የታጋይ ጳውሎስ ልዑክ ጳጳስ አቡን እንጦንስን፣ የታጋይ ጳውሎስ ስም የሚጠራበት ቤተክርስቲያን

ሂዳችሁ ቀድሳችኋል በማለት ልብሰ ተክህኖአቸውን ገፈው ከአውደ ምሕረቱ ያባረሯቸውን ካህናት፣ እንዲሁም የወያኔ እምባሲ አባላት በተገኙበት ይቅርታ ሲጠይቁ የሚያሳይ ቪዲዮ ነው።

http://www.youtube.com/watch?v=Y_AiNCXCl90&feature=youtu.be

ከዚህ በኋላማ፣ ሰውየው ጀግና ተባሉ! ሰማ'ዕት ተባሉ። ታጋይ ተባሉ! በወያኔ አሽቅባጮች ተጋብዘው፣ ከዚህ በፊት ለምን እዚያ ሂዳችሁ ቀደሳችሁ በማለት ያባረሯቸውን ካህናት ፊት፣ የሲኖዶሱ ወታደር ነኝ ብለው ደነፉ። "ያለው አንድ ሲኖዶስ ነው! እሱም ያለው አዲስ አበባ ያለው ነው" ብለው ምድረ ወያኔን፣ አሽቃባጭ ወጣት ሴቶቻቸው "እልል" አሰኙ፣ ምንም የማያውቁ ትናንሽ መዘምራኖቻቸን አስጨበጨቡ።

ይኽ በተደረገ ማግስት የወያኔው የሥላሴ በተክርስቲያን፣ ለትግሬዎች ብቻ ተብሎ በአባ እንጦንስ የተቋቋመው ቤተክርስቲያን፣ የጀማይካዎች ጸርሀ ጽዮን ቤተክርስቲያን እንዲሁም በአዎርፓ ደረጃ የተዋቀረው ሀገርስብከት መዕምናንና አባላት ተሰብስበው የለንደን ደብረጽዮን ቅድስት ማርያም ዋና አባላት በሌሉበት ዕጣ ፈንታችንን ከአፈንጋጮቹ ጋራ ስለኛ ወሰኑ። "ከዛሬ ጀምራ ለንደን ደብረጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲአይን የአዲስ አበባው ሲኖዶስ አካል ናት" ብለው ደመደሙት። የሰበካ ጉባኤም አቋቃሙ።

http://www.youtube.com/watch?v=JWuy5HIT-uk&feature=youtu.be

"አገቱኒ ከለባት" አለ ቅዱስ ዳዊት! ከኢትዮጵያ የመጡት ጳጳሳት የሠሩትን ሸምግልና አንድ ወንድሜ ሲያብራሩ፣ "ይኽ ባልና ሚስትን ለማስታረቁ የተላኩ ሽማግሌዎች፣ ባለጉዳዮችን ባልና ሚስትን ትተው፣ የማይወዷቸውን ጎረቢቶች ሰብስበው፣ ስለነሱ ትዳር ወስነው የሄዱ አላዋቂ ሽማግሌ አስመሎባቸዋል። "ነው ያሉት። መወያነቸው የሚረጋገጠው፣ በእንዲህ ዓይነት ኢትዮጵያዊ ስብሰባ ላይ አንዲት ብጣሽ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አለመኖሯ ነው። አሽታሮት የሌለበቱ ሰንደቅ ዓላማ መለጥፍማ ለወያኔ እጅ አለመስጠት ነው። ሲደብር! እዮጵያዊው በሙሉ አንቅሮ ተፋቸው። ኢትዮጵያዊ ሁሉ በተሰበሰበበት ግግም ብለው ሲሂዱ፣ አንድ ሰው ዞር ብሎ አላያቸው አለ። ጨርሶ ሕዝባችን ዘጋቸው። ወደ ወያኔ ዞር ነዋ! መንግስተ ሰማያት የለም ገሀነም ይጠብቃቸዋል!

ከጎናቸው ቁመው የሚጮኹላቸው ሜዲያዎች ቢኖሩ፣እንደ http://www.tigraionline.com/articles/article130264.html ያሉ ብቻ የወያኔ ሜዲያዎች ብቻ ናቸው

ይኽ ሁሉ ሲሆን፣ የሎንደን ክርስቲያናት፣ ወንዱም ሴቱም፣ ልጁም አዋቂውም፣ ቤተክርስቲያኑ ሕንጻ ጋ እየሄደ እሑድ እሑድ ልክ ቤተመቅደሳቸው እንደፈረሰባቸው ዕብራውያን፣ ጸሎቱን አቋርጦ አያውቅም። ታዲያ፣ ከሀዲው "አባ" ተባዩ፣ ይኽንን ክህደት በፈጸሙ ማግስት ዓይን አውጥተው ደረታቸውን ገልብጠው ለምን ቤትክርስቲያን ግቢ ሰተት ብለው አይመጡ መሰላችሁ። ዓይና አውጣ! ሕዝቡ ተናደደ። አይገቡም ብሎ በር ላይ ተጋፈጣቸው። "አባ" ተባዩ ፖሊስ ጠሩ። ፖሊስ ሲደርስ፣ አንድ ጣታቸውን ወደሕዝቡ ቀስረው፡ "This is my property! Please remove them?" ይህቺን ይወዳል የሎንደን ኢትዮጵያዊ! ከዚያ በኋላም ሴቱም ወንዱም እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ጥሬአቸውን ሊቆረጥማቸው ምንም አለቀረው። እዝህች ግቢ አትገባትም ተባሉ። አስወጡልን የተባሉት ፓሊሶች፣ ሜዳ ላይ የፈሰሰውን ሕዝባንን ሲያዩ እሳቸውኑ ከነደንገጦሮቻቸው ገፍትረዋቸው ከግቢው ውጪ ገተሯቸው።የሚከተለው ፎቶግራፍ የሚያሳየው አባ ተብዬውና ደንገጡሮቻቸው ውጪ ሁነው የሚያደርጉትን ሲዶልቱ ነው።



በዚህ ሁኔታ ቅጥሯ ግቢ ሳይገቡ ቀሩ። ሕዝቡ ጸሎቱን ከጨረሰ በኋላ ትምህርት ወደሚሰጥበት ትቶ ሂደ። ሕዝብ አይጥላህ! ሕዝብ ከጠላህ እግዚአብሔርም አብሮ ይጠለህል። ሳይበቁ መንኳሹ የመንደር አወደልዳይ (አዎን የመንደር አውደልዳይ - ለምን እንደተዳፈርኩና እንዳልኩ በመረጃ በኋላ ላይ አሳያለሁ) ያበጠውን ልባቸውን ሕዝቡ ላይ አሳይተው፣ ሕዝቡ አስተነፈሰላቸው። ብቻ ምን ያደርጋል፣ ውርደት ቀለባቸው ስለሆነ፣ በቃኝን አያውቁም። በዕውነትም ሕንጻው ንብረቴ ነው የሚል ደብዳቤ በሶሊሲተር አስጽፈው አምጥተውልናል። ቤትከርስቲያኗ፣ እሑድ-እሑድ መጥቶ ተገልጋይ እንጂ አባላት የሏትም በማለት ወደ ሁለት ሺህ የምንጠጋውን ምዕምን እንደሌለን ቆጥረው ደብዳቤ አጉርሰውናል።

በሚቀጥለው ሳምንት፣ ተከታዮቻቸው እንዲገቡ፣ እሳቸው ግን ሌላ ቦታ ሂደው ቀድሰዋልና (አርክሰዋል ካልተባለ) እንዳይገቡ ሊጋፈጣቸው ሕዝቡ ተስማምቶ ወደቤተክርስትያኑ ሂደ። ሕዝቡ ሲደርስ ፖሊስ ቦታውን ተቆጣጥሮት ጠበቀው። ሕዝቡ ከግራ በኩል ገባና ቅጥሩን ሞላው። እፍኝ የማይሞሉ የግሩም ደንገጡሮች፣ ከላይ ፎቃአቸውን ያያችኋቸው፣ ፖሊስ እየጠበቃቸው ቀኙን ያዙት። አሸከሮቻቸው ቦታውን እንደተቆጣጠሩት በስልክ ሲነግሯቸው፣ ግሩም ሆዬ ስልካቸውን ጆሮቸው ላይ ደቅነው እየተውረገረጉ፣ ወለም ዘለም እያሉ፣ እንደ አንበሳ ደቦር ጎምለል ጎምለል እያሉ መጡ። ግሩም መጣ! ግሩም መጣ ተባለ። ወይ መዋረድ! "አባ መጡ!" እንዳልተባሉ። ሕዝቡ ግር ብሎ ወደበሩ አመራና አንዴ በተቃውሞ በጩኸት ቦታውን አደባለቀው። እኔ ብሆን መሬቷ ተከፍታ ያኔውኑ እንድትውጠኝ በተመኘሁ ነበር። ሕዝብ ጠልቶኝ መኖርን አልሻም! ጌታ አምላኬ ሆይ እንደዚያ ከምዋረድ ቶሎ ውሰደኝ! ጉድ ፈላ። ሰውየው ሊያፍሩ? የባሰውን አይፎናቸውን (iPhone) አውጥተው ሕዝቡን ቪዲዮ እያነሱት በድፍረትና በንቀት ተጠጉት። የእግዚአብሔር ቁጣ ነደደባቸው። ከየት እንደመጣ፣ ማን እንደሚወረውረው የማይታወቅ (አንደረቢ -poltergeist የሚሉት ነገር ይሆን?) የዕንቁላል መዓት አባ ተባዩ አጭበርባሪ ግለሰብ አናት ላይ ይፈጠፍጥ ገባ። አሁንም ቢሆን አንድም እኔ ወረወርኩ የሚል ሰው አልተገኘም። እንቁላሉ ብቻ ዥው እያለ ሂዶ እራሳቸው ላይ ቷ ሲል ይታያል፣ ይሰማል! ቆባቸው ከላያቸው ላይ በረረችና ሂዳ ግንብ ሥር ተወተፈች! ይግርማል! ያ ሁሉ እንቁላል ሲወረወር አንድ እንኳን ስቶ ሊያተርፏቸው የሚሯሯጡትን ፖሊሶች አልነካም፣ "አባ" ተባዩን አሸትቶ ሂዶ ብቻ "ዷ!"። በሪሞት ኮንትሮል ከላይ የሚመራው (ጋይድ የሚያደርገው ሚሳየል) ተቀምጧል መሰለኝ። ተአምር ነው። ከየትም ትወርወረ ከየት፣ "አባ" ተባዩን እራስ የሳተ የለም ። ብቻ አንድ ወያኔ የቀጠረላቸው ጠረንገሎ ቦዲ ጋርድ (የውርደት ዘበኛ) ከሕዝቡ ጋር ሊጋፈጥ ሲሮጥ በፊቱ ላይ የፈነዳበት ዕንቁላል አስደንግጦት ወደ ኋሊት ተሰፈነጠረ። ፖሊስ ማንን ይያዝ። ሲመታ እንጂ ሲወረወር አይታይ! ጉድ እኮ ነው። "አባ" ተባዩ ባዶ ጭንቅላታቸውን በበሰበሰ የአንገት ፎጣቸው ምንተእፍረታቸውን ተከናነቡ። እሳቸውን ብሶባቸው "ሂጂ ካልተደባደብኩ" እያሉ ለፖሊሶችን አስቸገሩ። ግጥም አድርገዋቸው የያዟቸው ሴት ፖሊሶች እንደ ዕቃ ገፈታትረዋቸው አስቀሯቸው። እንዳስቸገሩ ቢቀጥሉ ኑሮ ሴቶቹ ፖሊሶች ከመሬት ፈጥፍጠው ሊቀፈድዷቸው ተዘጋጅተው ነበር። ብቻ እንደምንም ገፈታትሮዋቸው ከሕዝቡ አራቋቸው። አንዲት የሰውዬው ቅምጥ በባዶ ሜዳ ተነስታ እሪታዋን አቀለጠች። ደግነቱ አንድ ፖሊስ አጠገቧ ነበረና ማንም እንዳልነካት አይቶ ለሌሎቹ አስረድቶ የሆነ ሰው እንዲያዝላት አውቃ ያደረገችው መሆኑ ገባቸው።

## የአባ ተባዩ ቅጥር ጋንግስተሮች

በሚቀጥለው ሳምንት፣ ከዚያ ተቃውሞ በኋላ ሕዝቡ ምንም ዓይነት እንቁላልም ሆነ ድንጋይ እንዳይወራወር ተምምሎ እንደለማዱ ለጸሎት ብቻ ወደ ቤተክርስቲያኑ ሄደ።

የአባ ደንገጦሮች ከቷ በሚሆኑ፣ ታይተው በማይታወቁ ኩታሮች፣ አንድ ወንድም እንደገለጸው በኢንኩዩቤተር የተፈለፈሉ የሚመስሉ፣ ዋናው ሶሪያቸው ከግልገሏ ሱሪያቸው በታች ተንጠልጥሎ  የሚጆለጆል፣ ክርስትና በምንም ዓይነት ያልጎበኛቸው፣ ግማሹ ጨበሬ፣ ግማሹ ሹሩቢ በሆኑ፣ በአራዳ ቋንቋ "ፈልፈላዎች"፣ ኪሳቸው በሶስት ሶስት እንቁላሊችና ድንጋዮች ያባበጠ፣ ቁጥራቸው ከፍ ብሎ ጠበቀን። በኋላ በኋላ ላይ ስንረዳ፣ ግማሾቹ ወያኔ ለስለላ ከአዲስ አበባ ያስገባቸው፣ ግማሾቹ የይሑዳ አንበሳ የሚል ስም ሰጥቶቸው ሥርቻ ውስጥ ኳስ ሲጠልዙ እንዲውሉ የተፈረደባቸው፣ ሲሯሯጡ ውለው ሲመለሱ ቀፈታቸውን የሚሞሉትን አቅሮቦላቸው ወያኔ ለጥፋት የሚያሰለጥናቸው ዱሩዬዎች፣ ወይም ጋንግስተሮች መሆናቸውን ደረስናባቸው። ሕዝቡ፣ ከ"አባ" ተባዩ አደገኛ ሰው እንጂ ከነሱ ጥል ስላልነበረው፣ ዝም ብሎአቸው ለዕለቱ ትምህርት ወደተዘጋጀለት አዳራሽ ሄደ። እንቁላሉም፣ ሳይወረወር እንደታቀፉት ቀረ። ምናልባት ያን ቀን ታቅፈውት ስለዋሉ ማታ ላይ ጫጩቶች ካልተፈለፈሉ፣ ጠብሰው የሚያበሉትን እራት አገኙ ማለት ነው።

ስለነዚህ ጉዶች አንዲት አንጀት-አርስ ወጣት ፊስ ቡክ በሚባለው ወጣቶች በመሚወያዩበት መድረክ የሚከተለውን ጽፋ ወዳጆቼ አግኝተው  ላኩልኝ።

> ***"Hang-down Panty' youths straight from a thug fest – is this Ato Girum's (Ato Girma) idea of body-guards. These youths were clearly mis-informed and have been fed a diet of lies and were ready for some action and were told to go seek out and destroy 'your enemy'. Some of these youths with their bulging pockets, of eggs or stones, ready to hurl at a moment's notice. How the youths were so confused when they got there to find a short and peaceful demonstration which passed without incident. Even with that these 'high'***

***youths wanted to attack from behind, but were warned off by the police presence. It would have been good if they could have vented their frustrations on Ato Girum and his crews for lying to them.***

***Girum's confident swagger in the presence of his 'hang-down Panty' youth body-guards underlines that a priest who doesn't understand 'Blessed are the peacemakers, for they shall see the kingdom of God' is NO priest."***

*መጀመሪያ ላይ፣ "**"Hang-down Panty'*** አልገባኝም ነበር። ሰዎች እንዚያ የተንጠለጠለ ሱሪ የሚለብሱ መሆናቸውን ሲያስረዱኝ፣ ሆዴን እስኪያመኝ ነበር ከትከት ብዬ የሳቅኩት።

በሚቀጥለው ሳምንት፣ እነዚያኑ ወጣቶች ካናቴራ ገዝተውላቸው ከውስጥ አስለብሰዋቸው አመጡአቸውና ሊደበድቡን ሞከሩ። ተመልከቱልንማ!

http://youtu.be/l_K0GkT9SQs

በእንግሊዝኛ የሚጮኸው ሹሩቤ፣ ከሆነ ሥርቻ በኪራይ ከሳምንት በፊት ከመጡት፣ ሱሪአቸውን ከሙታንታቸው (ግልገል ሱሪ) በታች ከሚታጠቁት፣ ከአማርኛ ይልቅ የባዕድ ቋንቋ መናገር ከሚቀናቸው የወያኔ ቅልብ ጋንግስተሮች አንዱ ነው። የኛዎቹ ወጣቶችና ፖሊሶች በስንት ትግል ነው አደብ ያስገዟቸው። አደንዛዥ ዕጽ ያደነዘዛቸውን ጉብሎች፣ ለመደባደብ፣ "አባ" ተባዩ ገዝተዋቸው አመጧቸውና ሊያስደበድቡን ሞከሩ። ታዲያ እንዲህም ሁኖ፣ ጩኸቴን ቀሙኝ ሆነባቸውና፣ እሳቸው እራሳቸው "ተድበደቡኩ" እያሉ ያላዝናሉ። ምዕምኑን ዳሽቁ ካልገዛኹህ የሚሉ ሞገደኛ ሰው፣ እነሆ በገዛ ፈቃዳቸው ቤተክርስቲያናችንን ዘግተውብን፣ ቁልፉን ለወያኔ ወኪሎች በማስረከብ፣ ከአዲስ አበባ ድረስ አቡን በማስመጣት ለመንጠቅ ሞከረው ሕዝቡ ተረባርቦ ስለተጋፈጣቸው፣ የወጣላቸው አንድ ቁጥር ተስዳቢ ወጥቶአቸዋል።

# መንታ ሐሳዊ የመንኵሳት ቡድን

በቤተክርስቲያናችን ታሪክ፣ በደርግ ዘመን፣ ሁለት ሳይበቁ የመነኑ የመንኰሳት ቡድን ገዳሞቻችንን አትለቅልቀዋት ነበር። አንደኛው አገሪቷን ከገንጣዮችና አስገንጥዮች ላለመከላከል ገዳም የገባ ነው። ሊላው አገሪቱን ለመግንጠልና ለማስገንጥል ለማመቻቸት ገዳም የገባ አካል ነው። አንደኛው ቡድን፣ ከወታደራዊ ደርግ፣ ለጦርነት ዘመቻ ለውትድርና አስግድዶ ምልመላ ሲጀምር ለማምለጥ ወላጆች በሚያውቋቸው የቤተክርስቲያን ሹማንት አማካኝነት ወንድ ሎጆቻቸው ገዳም ገብተው እንዲያመልጡ የአመቻቹላቸው ሳይበቁ የመነኑ ኮብላዮች ናቸው። ሲጀመርም መነኰሳት አልነበሩም፣ ሲጨረስም ሳይሰበሩ ወጡ። ደርግ እስኪወድቅ ድረስ እዚያው እንጨት ሲሸከሙ፣ ውህ ሲቀዱ ኖሩ መነኮሳትን ሲረዱ ኖሩ። ከዚያም እንደመነኰሴ ተቆጥረው በኋላ ላይ ወደ ከተማ ተሰማሩ። የምንኩስና ሥርዓቱን ሲያገለግሏቸው ከነበሩት አባቶች በኩረጃ ተምረዋል፣ ውስጣቸው ግን ባዶ ቀፎ ነው። ሲጀመርም ደናግላን ላይሆኑ ይችላሉ፣ ስለዝህ የመነኰሴ የውሸት አክሴማ ያጥልቁ እንጂ ዕውነተኛ መንኰሳት አይደልም። የቀበሮ ባሕታውያን ናቸው። ቤተክርስቲያን አፍራሽ ፩ ቁጥር በሏቸው።

ሁለተኛው ቡድን፣ ወያኔ በረሀ እያለች፣ ለሶስትና አራት ዓመታት አሰልጥና ወደገዳም የሰደደቻቸው፣ አሁንም ስያበቁ የመነኑ በሺህ የሚቆጠሩ፣ ተዋጊ የወያኔ አስመሳይ የቀበሮ በህታውያን ካድሬዎች ናቸው። በመጀመሪያ ደረጃ፣ የደብረዳሞንና የዋልድባን ገዳማት የወረሩ ታማኝ የወያኔ ካድሬዎች ነበሩ። ከዚያም ሌሎች በሺህ የሚቆጠሩ በሌሎች የኢትዮጵያ ገዳማት ተበትነው፣ ቤተክርስቲያኒቱን ጨምድደው ያያዙ አራዊቶች ናቸው። ዶክተር አረጋዊ በርሄ ስለነዚህ ሰዎች ሲጽፉ እንዲህ ይላሉ፡

> ***To weaken church authority, an intelligence group was formed under Sibhat Nega to infiltrate the well-established monasteries in Tigrai, such as Debre Damo, by planting TPLF members camouflaged as monks and influencing church activities in the interests of the TPLF[3].*** (p 302)

ለሀያና ለሠላሳ ዓመት ገዳምና ትላልቅ አድባራት ውስጥ የካድሬነትን ሥራ እየሠሩ በመኖር፣ እራሳቸውን አደራጅተው፣ ዛሬ አንዳንዶቹ የጳጳስነት ሹመት ደረጃ የደረሱም አሉ። ምን ችግር አለ! ፓትርያርኩ የነሱ፣ አስተዳደሩም የነሱ! ወያኔ እስከፈለጋቸው ድረስ ከዚያም ያለፈ ማዕረግ መድረስ ይችላሉ። እንግዲህ እንደነዚህ ያሉት በቅጡ ሳይመነኰሱ የመነኰሱ መነኮሳት ናቸው በጭናቸው እሳት አዝለው እየተጓዙ ልጅ በየደረሱበት እየወለዱ፣ ቤተክርስቲያናችንን የሚበክሏት። ቤተክርስቲያን አፍራሽ ቁጥር ፪ በሏቸው።

---


[3] Berhe, Aregawi (2008) A Political History of the Tigray People's Liberation Front (1975-1991): Revolt, Ideology and Mobilisation in Ethiopia, Amsterdam, PhD Thesis.

ለመሆኑ፣ አባ ተባዩ ከየትኛው ወግን ናቸው? የጊዮርጊስን መገበርያ የበላ ሳይጠይቁት እንደሚለፈልፈው ሁሉ፣ እራሳትቸው ሲናገሩ እንደተሰሙት፣ ከበፊቱም ተደባዳቢ ሰፈር ያስቸግሩ እልኸኛ ሰው ነበሩ። እናታቸው ገዥው የወታደር መንግስት፣ ውትድርና እንዳይወሰዱባቸው ለተወሰነ ጊዜ ወደገዳም የወሰዷቸውና ከደርግ የሸሽጓቸው የሰፈር ውስጥ፣ ልክ እንደራስፑቲን አባ ጉልቤ ነበሩ። ሳይሰበሩ፣ ገዳም ገቡ። ሳይሰበሩ ወጡ! በኋላም አቡነ ገብርኤል ናቸው አሉ ወደ ኮሌጅ እንዲገቡ ውለታ የዋሉላቸው (አሁን በሚሰድቡት በስመ ወሎዬነት ማለት ነው)። ኮሌጅም እንደበጠበጡ መመረቅ አይቀርምና ዲፕሎማቸውን ይዘው ሲወጡ፣ በወንጌል አስተማሪነት አንዱ ቤተክርስቲያን (ገብርኤል ነው መሰለኝ) ተመደቡ። ቤተክርስቲያኑም ውስጥ ከአስተዳደሩ ጋር እየተጋጩ ስላስቸገሩ፣ አሁንም አቡነ ገብርኤል ለታጋይ ፓውሎስ ነግረውላቸው ከሊቀ ካኅናት ብርሀኑ ወለዓማኑኤል ጋር ሎንደን እንዲመጡና "ከአመጸኛው" ከለንደን ክርስቲያን እንዲፋጠጡ ላኳቸው። ሊቀ ካህናት ብርሀኑ ብቻቸውን ቀድመው መጥተው በመጡ በሶስተኛው ሳምንት ከሕዝቡ ጋር ይላተሙና ተዋርደው ወደመጡበት ይምለሳሉ። አለቃቸው ሊቀ ካህናት ብርሀኑ ከመመለሳቸው በፊት አቶ ግሩም ሆዬ ይመጡና አንዳንድ አባሎቻችንን አግኝተው እኛኛው ላይ የደረሰውን ውርደት ይሰማሉ። ዘዴ ቀይረው፣ ስምም ቀይረው፣ ታጋይ ጳውሎስን ያወግዙና ቁጭ ይላሉ። በሂደት፣ ከዚህ በፊት እንደገለጽኩት፣ ሕዝብ የሚወዳቸውን ቀሲስ ብርሀኑን ፈንግለው በ፰፰ ሰው ብቻ ተመርጠው አስተዳዳሪ ሁነው ጉብ አሉብን። እንግዲህ ተቀምጠን የሰቀልናቸውን ጉድ ናቸው አሁን ማውረድ አቅቶን ቤተክርስቲያናችንን በላያችን ላይ ጠርቀመው የሚጫውቱብን የቀበሮ ባህታዊ!

ታዲያ መነኮሴ ነኝ ይበሉ እንጂ አንድም የምንኩስና አይታይባቸውም። ቅዳሴውን ተውት! እንደመጡ ልክ እንደዛሬው ጸሕፈ ትዕዛዛቸው፣ ተሰጥዖም መመለስ አይችሉም ነበር። ብቻ አንዱ እንደምንም ቅዳሴ አስተምሮአቸው፣ ቄስ ሁነው ጉብ አሉ! የለየላቸው አለማዊ ናቸው። ምንም አይቀርቸውም። አንዳንዶቻችን ስንቀልድ፣ ምንኩስና እንዲህ እንዲህ እንደ አባ ግርማ ነጻ የሚያወጣ ከሆነ፣ ምናለ ሚስቶቻችንን እየፈታን እኛም እንሞንክስ እንጂ እየተባባልን እንቀላለዳለን።

## አባ ተባዩና ሴቶቻቸው

እያንዳንዱ መነኮሴ፣ በሶስት ዓመቱ ተመክሮ ጊዜ **<u>መጽሐፈ ምንኵስንና</u>** ሽምድዶ በቃሉ አውቆ በተግባር ማዋል እንደሚጠበቅበት




ካሕጻይ ገ/እግዚአብሔር የተበሉ ጸሓፊ አስነብበውናል። ብዚህ መጽሓፍ፣ ብዙ ብዙ ፍሬ ነገሮች ተዘርዝረዋል።

መጽሐፈ ሕግጋት ዓበይት (ፍትሕ መንፈሳዊን) በመጥቀስ ካንድ መነኮሴ የሚጠበቁ ከተባሉት መህል፡

- መነኮሴ ሹመት መውደድ አይገባውም፣ የሹመት ፍቅር ሰይጣናዊ በሽታ ነውና፣ በዚህ በሽታ ላይ የወደቀ ሰው ካህናትና ሹማምን ሊሆኑ በምግባቸው ላይ ቀናተኛ ይሆናሉ። (ቁ. 385)
- መጽሐፍ በጭኑ እሳት ቅጥሮ የማይቃጠል ማን ነው (ምስ 7፤ 27) ብሏልና ፈጽሞ ሴትን ከመቅረብና ከመነጋገር ይርቅ። (ቁ. 406)

"አባ" ተብዬው ግርማ ከበደ፣ እነዚሁን ሁለቱንም ሕግጋት ዓይናችን እያየ የጣሱ ሰው ናቸው።

የሴትን ድምጽ አትስማ እያለ፣ እሳቸው ድምጽ መስማት ሳይሆን አቅፈው ሲያሻሹ ቢታዩ የማይፍሩ ሰው ናቸው።

የገንዘብና የሹመት አውሊያ ይዞ እያጦዛቸው፣ እነሆ ከዚህ ሁሉ ሕዝብ ጋር ተጣልተው፣ ከአስተዳዳሪነቴ ከምወርድ፣ እዚህቺው እሞታለሁና፣ ስሞት ግን ወደ ኢትዮጵያ ሬሳዬን ላኩ ያሉ፣ ሞገደኛ ናቸው።

ሴቶችን በማሽኮርመም፣ የኛው አባ ተባዩና የራሺያው ራስፑትን አንድ ናቸው። የራሺያው ራስፑቲን አንዱ ባሕርይ፣ ሴቶችን አድኖ ማማገጥ ነው። ከንግስቲቷ ጀምሮ፣ አንድም የመኳንንቱ ሚስት አልቀረውም። የሚከተለው ፎቶግራፍ፣ ራስፑቲን በአፍቅሪ ሴቶቹ ተከቦ ማየት ይቻላል።



ምንጭ፦ http://altrapoint.com/2011/08/fascinating-characters-rasputin/።

ስለራስፑቲንም (http://www.ethiomedia.com/addis/rasputin_the_menacing_monk.pdfhttp://www.ethiomedia.com/addis/rasputin_the_menacing_monk.pdf: ከዚህ በፊት ስጽፍ አባ ጠንቀቅ እንዲሉና ሕዝቡን እንዲያከብሩት ላሳስባቸው ነበር። ጩኸቴ ጸሐይ ላይ ውሎ የጋመ ድንጋይ ላይ እንደፈሰሰ ዉሀ ሆነብኝ። በየቀኑ እየባሰባቸው፣ ጅብደኝነታቸው ስለበዛ ሁለተኛ መልዕክት ልልክባቸው ተገደድኩ። “አባባሱባትንም” http://ecadforum.com/Amharic/archives/6756/ ስጽፍ ሁልተኛ ማስጠንቀቂያዬ ነበር። እንኳን ሊያፍሩ፣ ዓይነ ያወጡ ተናዳፊ አውሬ ሁነው መጡ። እንግድህ ሶስተኛ ዕድል መስጠት የተለመደ ስለሆነ ሌላ መልዕክት ላኩባቸው። “ብጹአን አባቶች፣ ልታዋጉን ወይስ ልታስታርቁን መጣችሁ” http://ecadforum.com/Amharic/archives/7566/ ብዬ በጎን ስለአባና ሴቶቻቸው ጠቀስ ሳደርግ፣ የመጨረሻው ማስጠንቀቂዬ ነበር። አልሰሙም። የፍርዖንን ልብ ያደነደነው አምላክ የሳቸውንም ልብ ድንጋይ አድርጎባቸዋል። እንግዲያስ ውርድ ከራሴ! ይኸው ቦምቡ!

ሰለአቶ ግሩም የምንሰማው ጆሮ ጭው ያሚያደርጉ ናቸው። “አባ እንዲህ አሉኝ”፣ “አባ እንዲህ አደረጉኝ”፣ አባ “ቀሚስ ብለብስ ሴት መሰልኩሽ ወይ” አሉኝ የምትል ሞልታለች። “ዝም በይ” ተብላ ነው እንጂ አንዲት እስላም ቆንጆ ኢትዮጵያዊትም ለማሽኮርመም እንደሞከሩ ሰምትናል። ያም ይቅር።

አባ ፍሊፖስ የተባሉ ሊቀ ጳጳስ በ1961 “የምንኵስና ሥነ ሥርዓት ብያኔ” በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፍ፣ ገጽ 36 ላይ የሚከተለውን ብለዋል።

> ***ምንኵስና ማለት በዚህ ዓለም ከሚገኘው ምኞት፣ ከሥጋዊ ብዕልና ክብር ተለይቶ ፈጣሪ ጌታን በሥነፍጥረቱ እያሰቡ ከወዳጅ ዘመድ ርቆ፣ በራዕይ እና በሰማዕ ከሚገኘው ፍትወት*** በመሸሸ ***የሴት መልክ ከማይታይበት፣ ድምጹዋም ከማይሰማበት በርሀ ወደቀው በበአት ተከተው ከዓለም ተገልለው እግዚአብሔርን በጾምና በጸሎት በቁመትና በስግደት እየለመኑ በተባሕትዎ (በብቸኝነት) የመኖር ሕግ ማለት ነው። (ገጽ 36)***

መጽሐፉ፣ በማያወላውል መንገድ እንዲህ ካስቀመጠ፣ የኛ አባ ተባዩ፣ ይኸቺን የመሰልች ውብ ሊጋ ለግላጋ በጭናቸው መሀል አስቀምጠው፣ ጎፈሬ እያበጠሩላት ነው ወይስ ሹሩባ እየሡሩትላት ነው?



ምንጭ፦ https://www.facebook.com/photo.php?fbid=10200736641284147&set=a.1506022616272.67961.1405491890&type=1&theater

ለማንኛው ድንገት ካነሱት ብዬ የእስክሪኑን ፎቶ አንስቼዋለሁና ምንጩ አያሳስበኝም። ፎቶው ከመነሳቱ በፊት ሁላችሁም screen shot አድርጉት።

እንግዲህ መጽሐፉ፣ "ሴትን ድምጿን እንኳን አትስማ" ሲል እንዴት ሲደረግ ነው አቶ ግሩም ሆዬ፣ መነኰሴ ነኝ እያሉ ይኽችን የመሰለች ሸበላ ጭናቸው ውስጥ የሰገሰጓት? እንዴት አንገቷን ታፋቸው ላይ በፍቅር ዘንበል አድርጋ ፎቶ እንዲትነሳ የፈቀዱላት? እንዴት ሲደረግ ነው መስቀላቸውን ጭምድድ አርገው ይዘው አይኖቻቸው ጭልምልም ብሎባቸው፣ ልባቸው እንደተስለመለመ ፎቶ ለመነሳት የፈቀዱት? ልጅቷስ ምን ዓይነት ግድያ (ትሮፊ - trophy) ብትጥል ነው እንዲህ አይነቱን የግል ጉዳይ በምስጢር መያዝ ያለበትን (private) ፎቶግራፍ ሕዝብ ሁሉ ከሚያይበት ፌስ ቡክ ላይ በአደባባይ ልትለጥፍ የቻለችው? <u>መጽሐፈ ምንኵስና፡</u> ሴት ካለችበት አትድረስ ይላል፣ "አባ" ተባዩ ወጣት ሴቶችን ጭናቸው ውስጥ ከተው ሲያሻሹ እየባረኩ መልቀቃቸው ነው?

"አባ" ተባዩ እራስቸውን ብቻ አይደለም በአደባባይ ያጋለጡት። ወጣቶችን ሴቶች በሙሉ አሰልጥነው ከመነኰሴ ጋር መዳራት እንዳልተፈቀደ አላስተማሯቸውም። ከመነኩሴ ጋር መተሻሸት በረከት የሚያስገኝ መስሎአቸው እንደሆን እንጃ፣ ብቻ መነኰሴ፣ በተለይ ጳጳስ ባዩ ቁጥር ደቂቀ ግሩም ልባቸው ዘለል-ዘለል ትልባቸዋለች መሰለኝ፣ እየሄዱ ልጥፍ ማለት ሁኗል ሥራቸው። ይኸን

የሚያደእርጉት፣ የአባ ደንገጡሮች፣ የለንደኖቹ ወጣት ሴቶች ብቻ ናቸው። ከዚህ በታች፣ ፌስ ቡክ ፕሮፋየሏ ላይ የጣለቸውን ግዳይ ለጥፋ የምታሳየን ሸበላ፣ በየኢንተርነቱ፣ ለአባ ጥብቅና ቁማ በአለብላቢት ምላሷ የምታዋርደን ማራኪ የተባለች ልጅ ናት። ምንም ሳትፈራ በአሁኑ በፓትሪርክ ላይ ተለጠፋ እዩልኝማ!



ምንጭ፡- https://www.facebook.com/godlovemaki?ref=ts&fref=ts

የራሷ ፊስ ቡክ ፕሮፋይል። Foto Shoot አድርጌ save አድርጌዋለሁ። መረጃው የአደባባይ ምስጢር ነውና ከእንግዲህ መደበቅ አይቻልም። ለመሆኑ ነውር መሆኑን ታውቃለች? ብታውቅማ አታደርገውም! በፍጹም እንዴት ተደርጎ! ሰውየው "ከመንኩሴ ጋር መለጠፍ ምንም የለበትም" እያሉ አሻሽተው ያላመዷት ውሮ ትመስላለች!

ሌሎቻችሁ፣ ሕጉ እንኳን ለሴቱ፣ ለናንተም ለወንዱም አይፈቅድምና፣ እንዳታሰናክሏቸው ዕውነተኞችን አባቶች አትቅረቡ። ቅዱሳን ስለሆኑ አታርክሷቸው። ራቅ ብላችሁ መስቀሎቻቸውን ካሳለሟችሁ ተሳልማችሁ፣ እጃችሁን ወደኋል አጣጥፋችሁ መቆም ነው። በተለይ ሴቶች ተጠንቀቁ! "አባ" ተባዩ አላስተማሯችሁምና እንዲህ ስታስቡት ተደርጎ የማይታወቀን ነውር ሠርታችሁ፣ በድርጊታችሁ በጣም በመኩራታችሁ አደባባይ ለጠፋችሁ። እናንተ አንዲት ነገር አትሆኑም። ያ መሆን እንደሌለበት ላላስተማርችሁ ካህን ግን ወየውለት! ወየውለት! ወየውለት!

አንዷ ፣ አቡነ ግብሬል ብብት ሥር ልትወሸቅ መንም አልቀራትም። እንዲያ ሚስት መስላለች። አይ አቶ ግሩም!



ምንጭ፡ https://www.facebook.com/meryalex30?fref=ts

አቡነ ገብርኤል እንኳን ጥንቁቅ ነበሩ፣ ምነው "ወደዚያ ፈቀቅ በዪልኝ ልጄ፣ ታሳስቺኛለሽ" ብለው በድፍረት አልተቆጧት? እንዲያው ሂዶ ልጥፍ!! አይ ለንደን! ግሩም እንዴት አበላሹሽ ጃል። ልጅቷ ምንም የምታውቀው ነገር የለም። ኃጢአቱ እንዳለ በ"አባ" ተባዩ ትከሻ ላይ ነው የሚደፈደፈው! ሶኖዶስ! ዝም ትላላችሁ! ሎንደን ያስቀመጣችሁት ሰው "ማኖ" ወይም እጅ-እላፊ እያስነካችሁ ነውና አንድ ነገር በሉ!

ሌላዋ ደግሞ፣ በየእሑዱ ሽንጧን ገትራ ያለምንም ሀፍረት ሽማግሌዎችን የምታዋርድ ወጣት ሴት፣ አባ ቀውስጦሥስ ለምን ይቅርባቸው ብላ ነው መሰለኝ፣ እንዲሁ አንድ ሰሞን አንድ አሰገራሚ ፎቶግራፍ በፊስ ቡክ ፕሮፋይሏ ላይ ተጥቅማ ታዳሚውን አዝናንታለች። ጉድ እኮ ነው። እስቲ ተመልከቱት።



*ወየው ሀያማኖቴ! ውየው ኦርቶዶክስ ዕምነቴ! አልጋው ደግሞ ከኋላ ምን ያደርጋል?*

እነዚህ ወጣት ሴቶች፣ የሚያደርጉት በፍጹም በምንኩስና ዋና መመሪያ መጽሐፍ፣ **በመጽሐፈ ምንኩስና** እንደማይፈቀድ አያውቁትም። ተጠያቂው "አባ ግርማ ከበደ የተባሉ የቀድሞ ግሩም ናቸው።

ሴቶቹ በጣም ነው የሚያሳዝኑኝ። ግሩም ባሰለጠኗቸውና አቅሌሲያ ብለው በስየሟቸው አሽከሮቻቸው "የዕንቋላል ጦርነት ቁጥር ፩ እና ቁጥሩ ፪ ብለው የግጥም ናዳ በታላልቅ ኢትዮጵያውያንን ላይ ሲያዋርዱ፣ ለልጆቹ ስል ዝም ባልኩ ነበር። "እኚህ ሰው (አቶ ግሩም) ዓይን አፍጥጠው እየተጋፈጡን ነው። ብናጋልጣቸው የነዚህ ምንም የማይውቁ የዋህ ወጣት ሴቶች ስሜት ይነካል በማለት ጨንቆኝ ለወራት ቆይቼ ነበር። አሁን፣ የንሰሐ ኑዛዜአችንን እያወጡ መዘክዘክ ሲጀምሩ፣ ምን ላድርግ ብዬ አንድ አዋቂ ወዳጄን ባማክር፣ *"ሥጋ መሬት ከወደቀ፣ አፈር ማንሳቱ አይቀርምና"* አንዳችንም እንዳትምር" አለኝ። "አሁን ስሜታቸው ቢጎዳ፣ ትክክል አለምሆኑን ይረዱና ሌሎች ወጣት ሴቶች እንዲህ ዓይነት ስሐተት እንዳይሠሩ ጥሩ መካሪ ይወጣቸዋል" አለኝ። እህቶቼ፣ አቶ ግሩም ለራሳቸው ትክክለኛውን የምኩስና ሕይወት ሳያውቁት የገቡበት ስለሆነ የሚያደርጉትን አያውቅምና እናንተ ከስህተታችሁ ተምራችሁ ሌሎችን አስተምሩ።

እራሳቸው፣ የአሁኑ ፓትርይርክ ሆነው የተሾሞትን የአባ ማቲያስን ኢንተርቪው ብንሰማ፣ እንደ ግሩም ያሉትን የዘመኑን መንኰሳት ከሥር ይጠርቧቸዋል። እስቲ ስሟቸው! መስማት አይከፋም! ግድ የለም፣ በሞቴ ስሟቸው።

http://www.youtube.com/watch?v=CpeQ9wCEBTE&feature=share

አንድ መነኮሴ ሲሞነኩስ የሶስት ዓመት ተመክሮ እንደሚያስፈልገውና ተፈትኖ እንደሚያልፍ ሲሆን፣ ዛሬ ግን ከየመንገዱ እያመጡ አመንኩሰውት መላክ ነው ብለው፣ ፓትርያኩ ሳይቀሩ ተናግረዋል፣ ዳሩ ምን ያደርጋል፣ የግሩም ምልምል እሳቸው ሳያውቁት በ"አባ" ተባዩ ተልካ ጉድ አድርጋቸውለች!

ቀሲስ አስተርየ ጽጌ፣ የዘመናችን የቤተክርስቲያናችን ሊቅ፣ ይኸን ጉድ ሲያዩ ሳካፍላቸው፣ መጽሐፈ ምንኩስና ስለዚህ ምን እንድሚል በጃቸው ገልብጠው፣ ከነትርጉሙ ልከውልናል። እየቀነጫጨብኩ ባስገባ፣ የቁም-ነገሮቹን ውል ስቼ አበላሸዋለሁ በዬ በመስጋት፣ እንዳለ አቀርበዋለሁና፣ አንብባቢ አንብቦ ይማርበት!

*መጽሐፍት የሚሉት፡-*

*መነኩሴ ሥጋ ከበላ ከትህትና ይርቃል።* ከትህትና ከራቀ ምንኩስናው ፈረሰ። ሥጋ የከብትነት ኃይል ምንጭ ነው። የጉልበትሥራ የሚሰሩ ክርስቲያኖች፤ ኃይል ለማመንጨት ያውም ሳይበዛ ሥጋ ቢበሉ ይስማማቸዋል። ከሥጋው የሚያገኙን ኃይል በሚሰሩት የጉልበት ስራ ከሰውነታቸው ያወጡታል። መነኩሴ ደረቴ ይቅላ ሰውነቴም ይሙላ ካለለ በቀር ሥጋ መብላት የለበትም፤ ኃይሉን የሚያወጣባት ስራ ስለሌው በቀላሉ የሚፈነዳ ቮልካኖ ነው። ልቡ በትእቢት ያብጣል። በመቆጣት በመቁነጥነጥ በሚሰማው ሁሉ ነገር ሁሉ በሰው ላይ ይፈነዳል። የማሰቢያ አዕምሮውም በሞራ ይመረጋል። ኃጢአት ለማደን የበረታ ይሆናል። ለጸሎት ይደክማል። ስለዚህ በዓለም እየኖረ ይቅርና በገዳምም ያለ መነኩሴ ሥጋ መብላት የለበትም። ስጋ የማይበላበት ምክንያት ስጋ ርኩስ ሆኖ አይደለም። ልቡ በሞራ ተሸፍኖ በትእቢት እንዳያብጥ; የማሰብ አንጎሉም በሞራ እንዳይሸፈን፤ በሰው ላይ እንዳይፈነዳ ነው። ለጸሎት ከመትጋት ይልቅ ወደ ዓላማዊ ሀሳብ በማዘንበል የኃጢአት አዳኝ አውሬ ይሆናል **"ወኢይብላእ ሥጋ ለዓለም፡ አኮ እስመ ውእቱ ያረኩሶ አላ ከመ ኢይግዝፍ ልቡ ወኢይጽልም አዕምሮቱ ወኢይትከሀሎ ከመ ይትጋህ በዕረፍት (ፍነ ፳፡፻፳)"**

*መነኩሴ ከገዳም ከወጣ እግዚአብሔር ቀድሶ የሰራውን ወንድነት በማክበር የምትመስለውን አግብቶ መኖር አለበት።* የእንጦንስንና የመቃርስን ምንኩስና ምሳሌ ለመከተል ነው። የዓለማዊ ፍላጎት ጥማት ለማርካት ካልሆነ በቀር መነኩሴ ከገዳም መውጣት የለበትም። መነኩሴ ከገዳም ከወጣና ወደ ሌላ አገር ሄዶ የሚኖር ከሆነ፤ መነኩሴ ሆኖ፤ መነኩሴ መስሎ መኖር ከጀመረ ወደ አውሬነት የተለወጠ ሰው ነው። እንዲህ እንዳይሆን ከህዝቡ እንዳንዱ ሆኖ መኖር አለበት። ከገዳም ወጥቶ በህዝቡ መካከል ሲኖር በሚያሳየው የተሰባበረ ጸባይ ምንኩስና እንዲህ ነው እንዴ በሚሳኝ ባህርዩ የተቀደሰውን ምንኩስና ያስንቀዋል። ለእውነተኛው ምንኩስና ንቀትንና ውርደትን ያስከትላል። ይህም ብቻ አይደለም። እሳት በጭኑ ይዞ የማይቃጠል ማነው? ብሎ መጽሐፍ በጥያቄ እንደሚያስተምር፤ መነኩሴ ከገዳም ወጥቶ በህዝብ መካከል ከኖረ፤ በውስጡ ከተሸከመው የወንድነት ባህርዩ በራሱ ላይ የደፋው ቆብ አይለየውም። ፈጣሪ በውስጡ ያስቀመጠበት የህይወት ምንጭ ባህርዩ ወንድነት ነው። ይህ ባህርይው ለመጫር የተዘጋጀ እሳት ነው። የምትጫር የክብሪት ራስ ባህርይ ከሴት ጋራ ከተቀራረበ ሊያድፍነው ያምይችል እሳት ይጫራልና ከሴት አካባቢ ፈጽሞ መራቅ አለበት ። ወንድ ከሴትጋራ መገናኘት የተፈጥሮ ባህርይ ስለሆነ ባያስወግዘውም፤ ያልሆነውን ሆኛለሁ ብሎ በመቅረቡ ዋሽቷልን ከህብረተ ሰቡ መገለል አለበት። ሴቶችን ከመቅረብ እጅግ ይጠነቀቅ፤ ከመነጋገርም እጅግ ይራቅ ከገዳም አይውጣ ። **"ወለእመ ወጽአ እኁ እምኔቱ መኒኖ ህገ ምንኩስናሁ ወሆረ ሀበ ሀገር ውብሄር ከመ ይንበር ህየ ። ይኩን በመዓርገ ህዝባውያን እለ ሀለው ውስቴታ ወኢይደለዎ ሎቱ ከመ ይትመሰል በመነኮሳት ዘእንበለ አምሳለ ህዝባውያን። ለእመ ውእቱ ኢይክል ላዕለ ተጸውኖ አርእያ ምንኩስናሁ ይከውን ሐሜተ ሃበ ኩሎሙ መነኮሳት ወይሬሲ ሎሙ ስመ እኩየ ወዝንቱ አንቀጽ ዘእንበለ ግዘት" መጻህፍት ቅዱሳት ይሜህራነ መኑ ውእቱ ዘየአቁር እሳተ ውስተ ህጽኑ ወኢይውዒ" ከመ ንትገሀስ እምቀሪበ አንስት ፈድፋደ ወእምተናግሮቶን ተዓአቀቡ ጥቀ (ፍ አን ፲ ቁ፬፻፳ ፮)"**

*መነኩሴ ከገዳም ከወጣ ከዓለም ጋራ መተሻሸትንና መዳራትን ያስከትላል።* ከመቀራረብ የኃጢአት አይነት ያከማቻል። ውድቀት በምትከተው ሁለንተነዋ ላይ ያተኩራል; እሷም ትመለከተዋለች ምንኩስናው ፈረሰ። **'እምተዳድቆ ምግባራት ታስተጋብእ መዛግብተ ርኩስ። ወይኔጽራ ለጠባይዐ ምግባራት በነጽሮተ ዘማዊ; ማር ይስሐቅ ምዕ ፬**

*መነኩሴ ከገዳም ከወጣ፤ ሌላውን መክሮ አስተምሮ ከኃጢአት ሊያወጣ ቀርቶ፤ ራሱን ተጎትቶ ይገባበታል።* በመጨረሻም ተስፋ በመቁረጥ ተስፋ ወደሌለው አውሬነት ይለወጣል። የከተማ ኑሮ እሳትና ጭድ ነው። ሰውነቱ ላበጠ ጡንቻውን ላፈረጠመ ጎልማሳ ምንኩስና ለሥጋ ዊ ፈቃድ ለከተማ ኑሮ እሳት ነው። ከሥጋ ፈቃድ ራሱን ለመግዛት ብዙ ይቀረዋል። ሴትን በዓይነ ሥጋ መቃኘት፤ ይጀምራል። ቆብ የተሸከመበትን ጭንቅላቱን ካምበረከከች በኋላ፤ የተንበረከከበትን ጉልበቱን ትንተራሳለች። ስለዚህ ከጉልበት ሥራ መሸሽ፤ ጥሪት መሰብሰብ፤ ቤት ንብረት ማትረፍ፤ ሹመት መውደድ፤ በሌላው ላይ ከፍ ብሎ ለመታየት መጣር ራሱን ለዓለም ላስጎነበሰ ፤ ጉልበቱን ላንተራሰ ጎረምሳ እንጅ ምንኩስና አይደለም። **"ወኢያስተሐመሙ ለፈቂደ ጥዒና በእንቲአሃ። አላ ተክዕው ውስተ ባህረ ዝንቱ ዓለም በፈቃዶሙ ፈቲዎሙ ከመ ይፈውሱ ነፍሳተ ካልአን። ለሊሆሙ ድውያን አህጉሉ ርእሶሙ። ወቀብጹ ተስፋሆሙ እምተስፋ እግዚ። እስመ ድኩመ ህሊንና ኢይክል ተራክቦተ ነበልባል እስመ ዓዲሆሙ ጽኑሳን ኀበ ከዊነ ተዓቅቦ። ዘውእቱ እምርእየተ አንስት፤ አጥርየተ ነዋይ ወቆሳቁስ ሀሲሰ እረፍት ዘግብራት (ማር ይስሐቅ ምዕ ፳)**

*መነኩሴ ከገዳም ከወጣ በከተማ ከሚኖሩ ሰዎች ጋር መኖር ከጀመረ ያለ ጥርጥር ወድቋል።* ስለዚህ መነኩሴ ባመለካከት በፈቃድ በዓላማ እሱን ከማይመስሉት መራቅ አለበት። ራቅ። የሥጋ ፈቃድ መቀስቀስው ሚፈልቀው ከስጋዊ ንግግርና ጨዋታ ነውና ራቅ ተባለ። **"ዘእንበለ እለ ይመስሉ ኪያከ በፍናው ወክብር ወፈቃድ ወለብዎ ወተአቀብ እምተሳትፎ ዛውእ ነፍሳዊ ። እንተ በእንቲአሃ ይመጽእ ሁከት ወግብር። ወድህሬሁ ለፍጻሜ ዛውዕ አፍአዊ" ማር ይስህቅ ምዕ ፲፩**

*መነኩሴ አካሉን በጉልበት ስራ ካላደከመ፤። አዕምሮውን መጽሀፍ በማንበብ ካላደበረ ልጓም የሌላት በቅሎ ነው።* ፈቃደ ሥጋን አብርዶ ከበቁሎ ባህርይ ሊለይ የሚችለው ፤ አካልን በጉልበት ሥራ ማድከምና መንፈሳውያን መጻህፍትን በማንበብ ብቻ ነው። ይህንንም ተገንዝቦ ራሱን መጠበቅ የሚችለው መመሪያውን ሲረዳ ነው። **"ጻማ ሥጋዊት ወአንብቦ መጻሐፍት አምላካውያት**

**የዓቅብዋ ለንጽህና“እስከ ይመጽእ ብእሲ ናዛዚ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ለሊሁ ፡ይዔነስ ሀበ መጻህፍት አምላካውያት ከመ ይሰየም ውስተ ልቡ ተዘክሮ ሠናያት“ወትዜንዎሙ ለእለ ውስተ ገዳማት ወለእለ ተሌለዩ እምሰብእ””(”(ማር ይስ ፳፩) ፱፡፲፩**

መነኩሴ ሹመት ከወደደ ገንዘብ መሰብሰብ ከጀመረ ነፍስ ከመግደል አይመለስም። ሹመት የሚፈልገው ለመብላት ለመጠጣትና ለሥጋ ፈቃድ እርካታ እንጅ ለጽድቅ አይደለም። ሰው በነዚህ ፍላጎት ከሰከረ የሚቀረው ኃጢአት አይኖርም፤ መነኩሴ የክህነት ማእረግ አይፈልግ። ለገዳም አስተዳደር እንኳ ራሱን አያቅርብ።ሽመት መፈለግ ከሰይጣን የሚመጣ በህክምና የማይፈወስ በተህዋስያን ከሚመጡ የበሽታ አይነቶች የከፋ በሽታ ነው።ፍቅረ ሲመት የተጠናወተው መነኩሴ ቦታው በሚገባቸው ሊቃውንት ላይ በቅናትና ምቀኝነት ልቡ ይቃጠላል። ህዝቡን እያነሳሳ በሊቃውንቱ ላይ ያሳድማል። ያለ ችሎታውና አቅሙ ገንዘብ የሚመነጭበትን መንገድ ሁሉ ለመቆጣጠር በሚደርገው ስግብግብነት በተቃጠለ ምኞቱ ሹመቱ ለሱ እንደማትገባ ካወቀ ሰው ከመግደል አይመለስምና ከሱ እራቅ **“ኢይደለዎሙ ለመናኒ ከመ ይፍቱ ሢመተ ክህነት ወኢሊቀ ምኔት ። እስመ ፍቅረ ሢመት ደዌ ሰይጣናዊ ወዘወድቀ ውስተ ዝንቱ ሕማም ይከውን ቀናኤ ላዕለ እለ ይደልዎሙ ከመ ይኩኑ ክህናተ ወሥዩ ማነ ወይቀጽብ ሰብአ ላእሌሆሙ ወያስተናስእ ወየሐስስ ሞቶሙ ከመ ይኩን ውእቱ በመዓርጊሆሙ ወሶበ ኮነት ሎቱ ኢንኢድ ይከውን ማእከሌሁ ወማእከሎሙ ሁከት ( ማር ፲፡፫፻፹፩)**

ድሮ በሊቃውንት ትምራ የነበረች ቤተ ክርስቲያናችን በዚህ ዓይነት ባህርይ ባላቸው ሰዎች እጅ ላይ በመውደቋ ህዝበ ክርስቲያን እየታወከ ነው። ከዙ (zoo) ሰብሮ የወጣ አውሬ እስኪመለስ ድረስ መታወክ እንደማይቀር፤ ምንኩስና የወረረውን ከተማ እየለቀቀ ወደ ገዳሙ እስኪመለስ ድረስ ከከተማ ቆቡን እየገዛ ያጠለቀም ይሁን፤ ከገዳም የወጣም ይሁን ህዝቡን መስሎ በትዳር ካልኖረ ወይም ወደ ገዳሙ ካልተመለሰ ሀውኩ እየባሰ ይሄዳል። ትርምሱ እየባሰ ይቀጥላል። ይህ የመጽሀፈ መነኮሳቱ መመሪያ የሚለው ነው።

## ማጠቃለያ

የአቶ ግሩም ወጣት ሴቶችና ወንዶች የሚወርፉን፣ ሽሜ ጁጁ፣ ሽሜ ጉጉ እያሉን ነው። እየሄዱ የሚለጠፉባቸው መንኰሳት በዕድሜ የገፉ መሆናቸው አይታያቸውም መሰለኝ። ለማንኛው እኛ መሀል ያሉት ወጣቶች፣ በቁጥርም፣ በእውቀትም (ከኦክስፎርድም ሳይቀር በቅርብ የተመረቁ)፣ በችሎታም፣ በጉልበትም ያጥፏቸዋል። አለበለዚያም እሑድ-እሑድ ለጸሎት ስንሄድ፣ የግሩም ወጣቶች ጥለውን በላያችን ላይ በሄዱብን ነበር። ምንኛ ቢታወሩ ነው በዕድሜ የገፋነውን ብቻ እያዩ የሚሳደቡት። ዕውሮች! ፍቅር ዕውር ነው መሰለኝ። አንዷ ከኛ ጋር የሆነችና የተናደደች ወጣት፣ “እናንተ! ሂዱ! እኩያችሁን እየፈለጋችሁ ተዝናኑ! በዚህ ዕድሜአችሁ የቄስ ቅምጥ አትሁኑ “ ብላ በዚያው በፌስ ቡካቸው ነግራቸው ነበር። ግን አይሰሙሙ። አንድ መተተኛ ደብተራ ከቆሙሱ ጋር አሉ። በነዚህ ወጣቶች አፍዝ አደንግዝ ደግሞባቸው ይሆን? ለማንኛውም ሰይጣን ይስድብ እራስም አይደል? ከማን ይማሩ? ይስደቡን!

በነገራችን ላይ፣ ጳጳሳት መገልገል የነበረባቸው፣ ገና እሳትነት ዘመናቸው በሚያንቀለቅላቸው ወጣት ሴቶች ሳይሆን ሊዚሁ ጉዳይ በተላላኪነት በተመለመሉ፣ ቆሙሳት መሆን ነበረበት። ከአራት ዓመት ከአንድ ወር በፊት በጻፉት “ፈር የለቀቀ ቁምስና በቤተክርስያን ላይ የደቀና አደጋ” http://medhanialemeotcks.org/wp-content/uploads/2011/01/kumsina.pdf ሲሉ ቀሲስ አስተራየ በጻፉት ጽሑፍ፣ ቆሙሳት ከጳጳሳት ከተለዩ አደገኞች ሊሆኑ እንደሚችሉ አብራርተዋል። አቶ ግሩም ጳጳስም በሌለበት በባዶ ሜዳ ስለቆመሱ፣ ከአድገኝነትም የባሱ መርዘኛ መሆናቸውን በሎንዶን እያሳዩ ነው። ቀሲስ አስተራየ ትክክል ናቸው።

እንግዲህ ለንደን ውስጥ ያለነው፣ በሥጋም በነፍስም ፈተና ውስጥ ገብተናል። ወንድሞችና እህቶች በያላችሁበት ጸልዩልን። ወደ ሕግ ቦታም እየሄድን ነው። ክርስቲያኖች በያላችሁበት እየተወያያችሁ፣ በምክርም፣ በሀሳብም፣ በቁሳቁስም ታጋዮቹን ወንድሞቻችሁናን እህቶቻችሁን እንዴት መርዳት እንዳለባችሁ ተወያዩበት። የለንደኗን ደብረጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ከወያኔ ንጥቂያ የመትረፏ ትግል ሌላም ቦታ ላላችሁ ትልቅ መጽናኛ ሊሆናችሁ ይችላል። እዚህ ከተሸነፉ፣ ቅስማቸው ይሰበራል። ቤተክርስቲያናችንን ለማትረፍ የምናደርገው ትግል፣ የጠቅላላው ኢትዮጵያን ከወያኔ መንጋጋ ፍልቅቆ ለማውጣቱ የሚደረገው ትግል አካል ነው። ለንደንና አካካባቢዋ የምትኖሩ ስደተኞች ወገናችን! በአሁኑ ጊዜ ማንም ቤቱ መቀምጥ የለበትም። ሁሉም በነቂስ ወጥቶ ትግሉ ላይ ይሳተፍ። ከዚህ ጉድ ቤተክርስትያናችንን ለማዳን የሚደርገውን ጥሪ ሰምቶ መቀላቀል የግድ ነው።

እግዚአብሔር ይርዳን!!!